# ኢትዮጵያችን

***የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን***

**ኢትዮጵያችን ቅጽ** 5 **ቁጥር** 1 **ጥቅምት** 30 **ቀን** 2 **ሺህ** 13 **ዓ.ም.**

## <u>ዶክተር ዐብይ አሕመድ አሁንም ዕድልዎን ይጠቀሙበት</u>

***የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ*** *(* https://www.youtube.com/watch?v=BQSktzYFeaQ *)*

ዛሬ ዓለም ሰለጠነች፣ የሰው ልጅ በምርምርና ሥልጣኔ ጎዳና ተራቀቀ በምንልበት ዘመን ሰው በዘሩ እየተመረጠ በቢላዋ ሲታረድ፣ በቆንጨራና በሜጫ ሲጨፈጨፍ፣ እርጉዝ እናት ልጆቿ ፊት ስትታረድ፣ የተጨፈጨፉ አስከሬኖች ከገደል አፋፍ ሲወረወሩ፣ መንገድ ለመንገድ ሲጎተቱ፣ አካላታቸው ሲቆራረጥ ሌላም ሌላ እየተደረገ ይህ ለታሪክና ለትውልድ ተጥሎ ሲታለፍ እጅጉን ያሳዝናል። የሩቁን እንተወውና የቅርቡ አርባ ጉጉና በደኖን እልቂት ዘግበን ሳናባራ በላይ በላዩ እየጨመረ እነሆ ዛሬ እናትና ሕጻናትን ጨምሮ አዛውንቶችን ሰብስቦ በቦምብና በመትረየስ የመፍጀት እጅግ ዘግናኝ ድርጊት እየሰማንና እያየን ነው።

የኢትዮጵያን አገራዊ ሉዓላዊነትና የሕዝቧን አንድነት ለመበታተን አጀንዳውን በሕገ-መንግሥት አርቅቆ የሰጠን ህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ መርዘኛ ሠነዱን ይዘን አገር ልንለውጥ፣ ሕዝብን ወደ ዴሞክራሲያዊ ጎዳና ልናሻግር ከቶውንም እንደማንችል ደጋግመን ጽፈናል፤ አሁንም እንደግመዋለን። ኢትዮጵያ በዘርና በቋንቋ ክልል ተሸንሽና ከእንግዲህ የሚካሄደው የዘር ፍጅት እንደማይወገድ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ጊዜ እየጠበቀ በተቀነባበረ ሤራና ተንኮል የሚካሄደው በተለይ በአማራው ላይ ያነጣጠረው የዘር ፍጅት ከተጀመረ 28 ዓመታትን ሲያስቆጥር ዛሬ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሷል። ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ አገዛዝ እንዲሁም የወያኔ ሕገ-መንግሥት እስካለ ድረስ የዚህ የዘር ፍጅት የመጨረሻ ምዕራፍ እጅጉን ልንሸከመው በሚያዳግት ሁኔታ ሊከናወን እንደሚችል ሁኔታዎች ጠቋሚዎች ናቸው። በሁሉም አካባቢ የድረሱልን ጥሪ፣ የተከበናል እሪታ እየተሰማ ነውና።

“ችግራችን ከህወሓት አመራር እንጂ ከሕገ-መንግሥቱ አይደለም” ሲባል የኦነግን አጀንዳ ለማስፈጸም ካልሆነ ሌላ ለምን ተፈለገ? ወያኔ/ህወሓት በኢሕአዴግ ስም ይህን መርዘኛ ሕገ-መንግሥት ተገን አድርጎ ውስጥ ውስጡን አማራውን በዘር ማምከን ጭምር እየፈጀው፣ ቤተ ክርስቲያንን እያዳከመና እያቃጠለ፣ ምንሊክን ለማንቋሸሽ ሐውልት ያስገነባና ታሪክን እየበረዘ 28 ዓመት ሲገዛ የመጨረሻው ግቡ የዘር ፍጅት እንዲሆን ያዘጋጀውና ያቀነባበረው በሕገ-መንግሥት ከለላ ሥር ነበር፤ አሁንም ነው። በመሆኑም በአገራችን የተጀመረው የዘር ፍጅት እንዲያከትምና ኢትዮጵያ እፎይ ብላ፤ ሕዝቧም ድህነቱን በሰላም እንዲያጣጥም ከተፈለገ የዘርና ቋንቋ አከላለል ከነሕገ-መንግሥቱ ተንዶ የኢትዮጵያ አስተዳደራዊ አከላለል በሌላ መልኩ መዋቀርና ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት እንዲያብብ ከፍተኛ ርብርቦሽ መካሄድ ይኖርበታል እንላለን።

ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐብይ አሕመድ ይህን የወያኔ ሕገ-መንግሥት በመሻር ዘርና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል ያበቃ ዘንድ ሦስት ጊዜ ያገኙትን ዕድል አልተጠቀሙበትም፤ አሁን አራተኛውንና የመጨረሻውን ዕድል መጠቀም እንደሚኖርባቸው ልንጠቁም እንወዳለን። አለበለዚያ ግን ብዙ የአማራ ሕዝብና ሌሎች ብሔሮች ቢታረዱና ቢጨፈጨፉም የመጨረሻው አሸናፊ ኢትዮጵያዊነት ስለሚሆን የዚያ ጊዜ የወያኔ ሕገ-መንግሥትና ዘርና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል ብቻ ሳይሆን የሚቀበረው በሥልጣን እርከን ላይ ላላችሁትም ይብላኝላችሁ፣ የዚያን ጊዜ “ወየው ለእናንተ” እንደሚያሰኝ አትጠራጠሩ። ሕጻን ልጆቻቸውን ደረታቸው ላይ ታቅፈው በመትረየስ የተረሸኑ እናቶች ደም፣ ቤተሰብን እንዳለ ያጋየ ፍጅት፣ አዛውንት ሽማግሌዎችን ገድሎ የቆራረጠ አረመኔነት ወደድንም ጠላንም ሕገ-መንግሥቱ የሰነቀረው ከክልላችን ውጡ ጣጣ ነውና ፍትህ ይጠይቃችኋል።

ዶክተር ዐብይ አሕመድ ገና ሥልጣናቸውን እንደያዙ

1. “ኢትዮጵያችን!” ሲሉ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቁን አውለብልቦ ከዳር እስከዳር ዘርና ሃይማኖት፣ ዕድሜና ክልል ሳይለየው ለጮኸላቸው ሕዝብ ምንም ሳያመነቱ ኃይል የሕዝብ መሆኑን ተረድተው ሕገ-መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ የመቀየርና የዘርና ቋንቋ አከላለል ማብቃት እንዳለበት ወዲያውኑ ቢያሳውቁ በእርግጠኝነት የዛሬውን ዘር ተኮር ያደረገ ፍጅት የሚታሰብም አልነበረም።

2. የጠቅላይ ምኒስትርነቱን እንደተረከቡ መቀሌ ለመመሸግ ላኮበኮበው የህወሓት ወንበዴ ቡድን ዕድል ከመስጠትና ሁለት ዓመት ሙሉ እስኪጠናከር ከመጠበቅ እንደተርበተበተ በአፋጣኝ በቁጥጥር ሥር አውሎ ትግራይንም በመንግሥት መዋቅር ሥር ማስገባት ነበረባቸው።
3. ሌላው ለሁሉም ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች በሰላማዊ መንገድ ገብተው ከሕዝቡ ጋር እንቅስቃሴአቸውን እንዲያካሂዱ የዴሞክራሲ ጎዳና በጀመሩበት ወቅት የኦነግ ኃይሎች እስከ ትጥቃቸው እንዲገቡና በቀጣይነትም ወታደራዊ እንቅስቃሴና ልምምድ ሲያደርጉ እንዳላየ ማለፍ ሌላው ጥፋት ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ስህተቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ ለመጣው የዘር ፍጅት ከፍተኛውን አስተዋጽዖ ማድረጉ ሊታወቅ ይገባል።

ጠቅላይ ሚንስትሩ ሌላው ሁለተኛው ዕድላቸው የዓለም ኖቤል ሽልማት በተረከቡበት ወቅት የአገሪቷ መሠረታዊ ችግር የሆነውን ሕገ-መንግሥት በመሠረዝ አገሪቷን አዲስ ሕገ-መንግሥት እስኪረቀቅ በጊዜያዊነት የማስተዳደር ሂደታቸውን ተግባራዊ ቢያደርጉ ሥርዓት ልብሱ የሆነው ሕዝባችን ከነድህነቱ እንዴት ባስደሰታቸው። "አውቆ የተኛን. . ." ነውና ሊያደምጡ አልፈለጉም።

ሦስተኛው ዕድላቸው ቀደም ሲል በአሸባሪው ጃዋር ሞሐመድ ምክንያት ሕይወታቸውን ባጡ 96 ዜጎች ሳቢያ እንኳን ሕገ-መንግሥት ላይ ሊያተኩሩ ይቅርና ግድያውንም በዘር ቆጠራ አስረድተውን ጃዋርን "ወንድሜ" በማለት ሲሳለቁብን ከሕዝብ ጋር ያላቸውን ድጋፍ እየሸረሸሩት መምጣት ጀመሩ። ይህ ከፈጣሪው በቀር አለኝታ የሌለው ምስኪን ሕዝብ ፀሎቱን ሰሚ አላጣምና በራሳቸው ላይ ሲመጣባቸው ነፍሱን ይማረውና በሀጫሉ ሞት አስታከው ጃዋር ከአገርና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ አምላክ ሳይታሰብ መነቀረው። በዚህ ወቅት የዘረኝነት አባዜ ድብቅ አጀንዳቸው ካልሆነ ለሦስተኛ ጊዜ ይህንን ዕድል ከመጠቀም ይልቅ ይባስ ብለው "ጦርነት አውጃለሁ" ብለው ቂም የያዙበትን ምስኪን እስክንድር ነጋን ከአሸባሪው ጃዋር ጋር በአንድ ስም ለእሥር ሲዳርጉት ያተረፉት ቢኖር ከወጣቱና ከሕዝብ ዘንድ ያላቸው ድጋፍ ዝምታ ብቻ መሆኑ ነበር።

በነዚህ ሁሉ ሂደቶች እውን በኢትዮጵያ መሠረታዊም ሆነ ጥገናዊ ለውጥ ለማምጣት በምንም መልኩ ዘርና ቋንቋን ተገን ያደረገ አከላለል ተይዞ እንደማይሆን ጽፈን አስነብበናል። አሁንም የምንደጋግመው ከእንግዲህ ወዲያ ጊዜ እየጠበቀ ለሚደርሰው ዘር-ተኮር ፍጅት ተጠያቂዎች ለፍርድ ይቅረቡ ጩኸት፣ በሰልፍና መግለጫ ማውገዝ ሳይሆን መፍሄው ተግባራዊ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ለመጠቆም የወደድነው ከንጹሀን ፍጅት፣ ከእናቶች፣ ከሕጻናት፣ ከአዛውንት አባቶች፣ ከወጣቶች ፍጅት በላይ ምን ሊመጣ ይፈለጋልና ነው?

ጥቅምት 22 ቀን 2013 ዓ.ም. በወለጋ ክፍለሀገር ጉሊሶ ወረዳ ልዩ ስሙ "ጋዋ ጋንታ" በተባለው አካባቢ እጅግ ሊታመን በማይችል መልኩ በቦንብና በከባድ መሳሪያ በመታገዝ ለተደረገው ፍጅት ገና ከመግለጫው የሞተውን ሰው ቁጥር በትክክል ለመግለጽ ሲርበተበቱ ጀምሮ፣ የመከላከያ ሠራዊት ከአካባቢው መውጣት ምስጢር፣ የመንግሥት መዋቅር ባለበት አካባቢ አንድ አሸባሪ ቡድን ነዋሪዎችን ስብሰባ ሲጠራ፣ ሲሰበስብ፣ ሊገድል ሲዘጋጅ ዝምታን የመረጠ የመንግሥት አካል ምስጢር፣ የተፈጁት አማሮች መሆናቸው በራሱ የዘር ፍጅት መሆኑን ላለማመን እስከዛሬ የሚደረገው ዳርዳርታ ሁሉ ሲመረመር መንግሥት እራሱ ቀጥተኛ ተጠያቂ የሆነበት ወንጀል መሆኑን አበክረን የምንናገረው ይሆናል።

ይህን ድርጊት ህወሓት፣ ኦነግ፣ ሌላ የውጭ አካል አቀነባበረው አላቀነባበረው አገር እያስተዳደረ ያለው መንግሥት የሰላም ምኒስትር እውን የሰላም እንቅልፍ ላይ ነበርን? ያሰኛል። በሰለጠነው አገር ቢሆን በዚህና ከዚህ በፊት በተካሄዱ መሰል ፍጅቶች የሚመለከታቸው ቀጥተኛ ኃላፊዎች ሳይውል ሳያድር እራሳቸውን ከያዙት የኃላፊነት ቦታ ያገላሉ። የእኛ ትንንሽ ንጉሦች ግና ማን ነካቷቸው? የድሮው አምባገነን ገድሎም ያቅራራብን ነበር፤ የዛሬው ደግሞ እያለቀሰ ይቀብርልናል፣ እየገደለ መጽናኛ ይለግስልናል፣ አስገድሎም ሐውልት ያቆምልናል፤ አይ ኢትዮጵያ ስንቱን ያሳይሻል!

ዶክተር ዐብይ አሕመድ የዚህ የዘር ማጥፋት ግድያ ከባድነቱ የሚያስነሳውን ጥያቄ በመረዳት በቀጥታ "ወያኔ ተኮሰብን" በሚል ከህወሓት ጋር ጦርነት ጀምረዋል። እውን ሁለት ዓመት ተጠናክሮ እንዲቀመጥ እሹሩሩ የተባለለት ይህ የህወሓት ቡድን 28 ዓመት ሙሉ በአገር ላይ ለሠራው ዘረፋና ወንጀል፣ የንጹሃን ደም እጅጉን ተጠያቂነቱ አጠያያቂ አልነበረም። ጠ/ሚንስትር ዶክተር ዐብይ በሚመሯት ኢትዮጵያ የኦነግ ኃላፊዎች እየተመላለሱ ከወያኔ ምክክር ሲያደርጉ፣ ሠራዊታቸውን ሲያሰለጥኑና ሲያደራጁ፣ እነ ጃዋር ሕዝብ ላይ ሲጨፍሩ፣ ቄሮዎቻቸውን ሜንጫና ገጀራ ሲያስታጥቁ እውን የሚተክሉት ችግኝ ጋርዷቸው ነበርን? የህወሓት ባለሥልጣናት ያለምንም ጥያቄ ለፍርድ መቅረብ የሚገባቸው በአገርና ሕዝብ ላይ በሠሩት ወንጀል ነው። በዚህ ሂደት እውን ዶክተር ዐብይ በተጀመረው ጦርነት አሸናፊ ሁነው ቢወጡም የኢትዮጵያን ችግር ይፈቱታል ማለት አይደለም። አካሄዳቸው ከአንድ ዘር የበላይነት ወደ ሌላኛው ቤተመንግሥቱን ማገላበጥ ነውና የያዙት፤ አሁንም በድጋሚ መርዘኛው የወያኔ ሕገ-መንግሥትና የዘርና ቋንቋ አከላለል ካልተወገደ አገዛዛቸው የትም እንደማይደርስ በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን። ዘርና ቋንቋን ተገን ያደረገ አገዛዝ ከበቂ በላይ

ለ28 ዓመት በኢትዮጵያችን ላይ ያስከተለውን ውድቀት፣ በሕዝባችን ላይ የፈጠረውን ጭንቀትና ስጋት ከሞት ጋር አስተናግደናልና ያለምንም ማወላወል ማብቃት ይኖርበታል።

የደርግ አገዛዝ ተቃዋሚ የሚባል እንዳይኖር የዛሬ 43 ዓመት ገደማ በመላ ሀገሪቷ ባካሄደው ቀይ ሽብር ኢትዮጵያ ልጆቿን ተነጥቃ ጠንካራ የአንድነት ኃይል ለዓመታት በመመታቱ ለወያኔና ሻቢያ ወለል ብሎ የተከፈተላቸው በር ወያኔን ምንሊክ ቤተመንግሥት ሲያስገባ ኤርትራን ከአሰብ ጋር አስገንጥሏል። ወያኔና ሻቢያ ሥልጣን ጨብጠው ለ14 ዓመት በአገሪቷ ጠንካራ የአንድነት ኃይል እንዳያንሰራራ በጋራ ዳግም ዘመቱበት፣ ዘረኝነትን ከመትከል አልፈው አበለጸጉት። ጥንት በአንድነቱና በኢትዮጵያዊነቱ ከቶም ጥያቄ ያልነበረው የተማረ ኃይል ሳይቀር ዘሩን ፈላጊና “ምን የአንድነት ኃይል አለ” እያለ ማጥላላት ውስጥ እስኪዘፈቅ ድረስ በውጭው ዓለም ተጫወቱበት። ኢትዮጵያን አለኝታ አሳጧት። ለአገሩና ለሰንደቅ ዓላማው ሟች ትውልድ እንዳያንሰራራ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተቀጠቀጠ። ሕጻናት ከልጅነት ጀምሮ በየትምህርት ቤቱ የዘረኝነትን ልክፍት ሲሰበኩ አድገው፣ ሲሰበኩ ደነዘዙ። የዚህ ሁሉ ሤራ ኢትዮጵያን እስከቻሉ ድረስ በዘርና ቋንቋ ከፋፍለው መዝረፍና መቦጥቦጥ ሳያመቻቸው ሲቀር የቀበሩትን ፈንጂ ማቀጣጠል፤ ይህ ነው ከሥልጣን ዘመናቸው ጀምሮ ለዶክተር ዐብይ አሕመድ የተተወው አጀንዳ።

ጠ/ሚንስትር ዶክተር ዐብይ አሕመድ አሁን ያገኙትን አራተኛና የመጨረሻ ዕድል መጠቀም ይኖርባቸዋል። በጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም. ንግግራቸው “መቶ በመቶ የወያኔን ጥቃት ደምስሰናል” እንዳሉት እውነት ለኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝባችን እድገትና ብልጽግና ከሆነ ጉዟቸው የጦር መሣሪያቸው ወደ ካምፑ ሳይመለስ ሕገ-መንግሥቱ ላይ በመዝመት የዘርና ቋንቋን አከላለል ያለምንም ማመንታት መናድ እንደሚገባቸው አበክረን ልንመክራቸው እንወዳለን። ከእንግዲህ የእናቶች፣ የሕጻናት፣ የሽማግሌዎች፣ የወጣቶች፣ የሴቶች ደም እየፈሰሰ፣ እየታረዱ፣ እየተቆራረጡ፣ ሜጫና ገጀራ እየተውለበለበ፣ ቤትና ንብረት እየተቃጠለ “ኢትዮጵያዬ” እያልኩ እቀጥላለው ብለው እንዳያስቡት። ሁሉም እራሱንና አካባቢውን ለመከላከል በግልና በቡድን ወደ በቀል እርምጃ የተሸጋገረ እለት ሊወጡት እማይችሉት ጭንቅ ውስጥ ሊከታቸው እንደሚችል አስቀድመን እንጠቁማለን፡፡ ሁሉም ከአምላኩ ጋር የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ እንደደረሰ ይረዱት ዘንድ አግባብነት አለው። በኢትዮጵያ የዘር ፍጅት ከተጀመረ ከረምረም ብሏል፡፡ ይህንን የዘር ፍጅት መመከቱ በለቅሶና በጩኸት ብቻ ይቀጥላል ብለን ተስፋ አናድርግ። አገር ስንል ሕዝብ ነውና ለሕዝብ ሕይወት ቀዳሚ ያልሆነ መንግሥት ሸንገላው ሊያበቃ ይገባል። ስለዚህ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመው፣ በምክር ቤቱ የተጀመረውን ዕምባ ማፍሰስ ተመልክተው የችግሩ ምንጭ ሕገ-መንግሥቱ ነውና ነቅለው ሊጥሉት ካልቻሉ አይጠራጠሩ አብረው ይወድቃሉ። ***“ኢትዮጵያ አትፈርስም” ስንል አፍራሿ የወያኔ ሕገ-መንግሥት ነውና ሲናድ ይዟቸው የሚሰምጠው አጃቢዎች አሉት። በድህነቱ ተሳስቆ፣ ተጋብቶ፣ ተዋልዶ፣ የትም ሄዶ፣ የትም አድሮ፣ የትም ሠርቶ፣ አብሮ ጨፍሮ፣ አብሮ አልቅሶ፣ አብሮ ተምሮ፣ አብሮ ነግዶ፣ አብሮ ሠርቶ፣ አብሮ በልቶ፣ አብሮ ተጫውቶ፣ አብሮ ዘምቶ፣ አብሮ ጠብቆ፣ አብሮ ሞቶ፣ አብሮ ታሪክ ሰርቶ የኖረ ሕዝብ ደንቃራ ሆኖ የከፋፈለው የዘርና ቋንቋ ክልል የተደረመሰ ለታ ያቀፉትን ጠራርጎ ስለሚሄድ “ከዚህ ይሰውረኝ” ለማለት ቁልፉ አሁንም በእጅዎ መሆኑን እንጠቁማለን።***

በመሆኑም አሁን ኢትዮጵያ የተደቀነባትን አደገኛ የዘር ፍጅት ለማምከንና የተጀመረው የእድገትና ብልጽግና ጉዞ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ከተፈለገ

1ኛ/ ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐብይ አሕመድ የኢትዮጵያ አንድነትን ባስጠበቀ መልኩ አዲስ ሕገ-መንግሥት የሚረቀቅበትንና ለሕዝብ ግልጽና ነጻ ውይይት ተደርጎ ሊጸድቅ የሚችልበትን አፋጣኝ አቅጣጫ በመቀየስ ሕገ-መንግሥት አርቅቃቂ ኮሚሽን በማቋቋም ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድ እንጠይቃለን።

2ኛ/ የዘርና ቋንቋ አከላለል ሙሉ በሙሉ ያበቃ ዘንድና ኢትዮጵያ በሌላ አስተዳደራዊ መዋቅር ትካለል ዘንድ እንደ ምሳሌ ከዚህ በፊት በአቀረብነው (http://www.ethiopiachen.org/images/pdf/Eth_Vol3/040911_1H1H_Ethiopiachin_Vol_3_Leyultem_No_1.pdf) ተፈጥሮአዊ አቀማመጥን ጨምሮ ሌሎች አከላሎችን ከባለ ሙያዎቹ ጋር በመምከር የሚያጠና ኮሚሽን በማቋቋም አፋጣኝ እርምጃ ይወስዱ ዘንድ እንጠይቃለን።

3ኛ/ የዘርና ቋንቋን አከላለል አስታኮ በዘር፣ በሃይማኖት እና በጾታ የፖለትካ ድርጅት መደራጀት ክልክል መሆኑን በሕግ መደንገግ።

4ኛ/ “እዩዬ ሲዳላ ነው” እንደተባለው በግንቦት ወር 2013 ዓ.ም. የታሰበው ምርጫ ለሕዝባችን ከሕይወቱ በላይ አይደለምና ቅንነቱ ከአሎት አሁንም ምርጫውን በማራዘም ለጊዜው አገሪቷን በአስቸኳይ ጊዜ አስተዳደር ውስጥ በመምራት ሕገ-መንግሥት የመቀየርና ዘርና ቋንቋን ማዕከል ያደረገውን አከላለል ማብቃት ላይ ትኩረት ሰጥተው ኢትዮጵያን ወደ አዲስ ምዕራፍ ሊያሻግሩ ዕድልዎን ይጠቀሙበት እንላለን።

5ኛ/ አገሪቱ ስትረጋጋም ከምርጫ በፊት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ይደረግ ዘንድ ተገቢ ነው። የሕዝቡን ብዛቱን፣ ስብጥሩን፣ ስርጭቱን፣ ወዘተ. ማወቅ ከሌሎች የልማትና ዕድገት ዕቅዶች ጠቀሜታው በላይ በፖለቲካው ውስጥ የዴሞክራሲ ወይም የሕዝብ አስተዳደር መሠረት ነውና ከምርጫ በፊት የሕዝብ ቆጠራ ቅድሚያ እንዲሰጠው እናሳስባለን።

እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥትዎ አዋጅ ቢያወጣ አይጠራጠሩ ታሪክ እንደሚሠሩ፣ ዳግም ድጋፍዎ በአራቱም ማዕዘን እንደሚያስተጋባ። አይጠራጠሩ የሕገ-መንግሥቱ መወገድና የዘርና ቋንቋ አከላለል ማብቃት ከሕዝብ አንጻር የኦሮሞ፣ የትግራይ፣ የአማራ፣ የቤኒሻንጉል፣ የአፋር፣ የሶማሊያ፣ የሲዳማ፣ የወላይታ፣ የጉራጌ፣ የጋምቤላ፣ የአዲስ አበባ፣ የሁሉም የሁሉም ፍላጎት እንደሆነ። ከላይ ሁነው ሲያተራምሱን ቀን ተሌት እንቅልፍ ለሌላቸው አጥፊና በታች ፖለቲከኞች ከቶም አይጨነቁ።

ይህንን ተግባራዊ የማድረግ ፍላጎት ከሌልዎ አይጠራጠሩ ኢትዮጵያ የማትፈርሰው ሕገ-መንግሥቱን ንዳ የዘርና ቋንቋን ድንበር አንኮታኩታ ነውና ለዚህ ደግሞ "ምን እንዳያመጣ" ተብሎ የሚናቀውና የተናቀው ሕዝባችን እምላክ እንዴት እንደሚያስተካክልለት የሚያውቅ ማንም የለም። ይህንን ብናውቅ መለስም ባልሞተ፣ ወያኔዎችም ብን ብለው መቀሌ ባልገቡ፣ እርሶም ለስልጣን ባልበቁ።

መንግሥቶ ከላይ በተገለጹት የሕገ-መንግሥትና የዘርና ቋንቋ አከላለል ጉዳይ የአቋም ለውጥ ሊያደርግ ካልተዘጋጀ

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ያላችሁ በንጹሃን ደም መጠየቅን የማትፈልጉ እራሳችሁን ከተቀመጣችሁበት መቀመጫ በማግለል ከአገርና ሕዝብ ጎን ሰልፋችሁን አሳምሩ።
2. የምኒስትሮች ምክር ቤት አባላት በሙሉ ከዚህ የዘር ፍጅት ተጠያቂነት እራሳችሁን ለማዳን ሥልጣናችሁን በመልቀቅ ለዚህ ምስኪን ሕዝብ አጋርነታችሁን አሳዩ።
3. የምርጫ ቦርድ አባላት በሙሉ በዚህ ሁኔታ ሀገሪቷ እየሄደችበት ላለው የዘር ፖለቲካ የሞከራችሁት ጥረት የትም እንደማያደርስ የየወቅቱ ፍጅት ምስክር ነውና ሙሉ በሙሉ እራሳችሁን በማግለል "ዘረኝነት ይብቃ" በሉ።
4. በአገር ቤት የምትንቀሳቀሱ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ምንም ኃይል ለሌለው ሕዝባችን ኃላፊነት አለባችሁና ሲፈጅ እያያችሁ አቅም የላችሁምና ሞቱን ልትከላከሉለት አልቻላችሁም፡፡ ግና ጠንካራ ኃይል አላችሁ፤ መጪውን ምርጫ ሙሉ በሙሉ ባለመሳተፍ ብልጽግና ፓርቲ ብቻውን ይዋኝበት ዘንድ በመልቀቅ አሁንም ሊታረዱና፣ ሊጨፈጨፉ ለታሰቡት ወገኖቻችን አለንላችሁ በሏቸው።

ከላይ የተጠቀሳችሁት አካላት ይህን እርምጃ በጋራ ከወሰዳችሁ ጠ/ሚንስትር ዶክተር ዐብይ ብቻቸውን እንደሆኑ እንዲገነዘቡና የትም እንደማይደርሱ ጫና ልታሳድሩ ትችላላችሁ እና ሞት እበሩ ላይ ለቆመው ሕዝባችን የድረሱለት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ጆሮ ያለው ይስማ! የወያኔ ሕገ-መንግሥት የመጨረሻው ደረጃ የዘር ፍጅት ነው፡፡ የዘርና ቋንቋ አከላለል የመጨረሻው ደረጃ ኢትዮጵያን መበታተን ነው። ሁለቱም ተግባራዊ እንዳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመካበት የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ የተጠናከረ ኃይል የለውም። በድህነትና ትውልድ በመቅበር ተጫውተውበታልና። ግና ማንም የማይመከተው፣ ማንም የማያስበው ትልቅ እጅግ ግዙፍ ኃይል አለ፡፡ ኢትዮጵያ ወደ እግዚአብሔር የዘረጋችው እጇቿ መጨበጫውን የሚያውቅ የለምና የሕጻናት ዋይታ፣ የእናቶች ልቅሶ፣ የአባቶች እግዞይታ፣ የወጣቶች ልመና ትንሳዔዋን ያቀርበዋል። "ኢትዮጵያን አትንኳት" እንዳሉት ነብዩ መሐመድ ኢትዮጵያ እና ሕዝቦቿ እንዳይነኩ ለዔሊ ከለላ ያደረገ አምላክ ይከልላታል።

ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ፈጣሪ ይጠብቅ!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ

ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም. (November 08, 2020)

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «*ኢትዮጵያችን*» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጬት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin